እንኳን ለነቢዩ መሐመድ(ሰዐወ) የልደት በዓል (መውሊድ) በሰላም አደረሳችሁ።

የመውሊድ በዓል መጠራታችንን የምናስብበት ቀን ነው። ነቢዩ መሐመድ (ሰዐወ) የመጡበትን ተልዕኮ፤ የሠሩትን ሥራና ያመጡትን ውጤት እናስባለን።

ሰው ዝም ብሎ ወደ ዓለም አይመጣም። ተልዕኮ አለው። ታላላቅ ሰዎች የምንላቸው ሁሉ የመጡበትን ተልዕኮ ያወቁ፤ ዐውቀው ተልዕኳቸውን ለማሳካት የሠሩ፤ ለተልዕኳቸው ስኬትም ተገቢውን መሥዋዕትነት የከፈሉ ናቸው።

የነቢዩ መሐመድ (ሰዐወ) መምጣት ዓለምን በፊት ከነበረችበት መልክና ጠባይ ቀይሯታል። መምጣታቸው የዓለም ታሪክ መከፈያ ሆኗል። በዘመናቸው መሥራት ያለባቸውን ሥራም ሠርተዋል።

ለምን ወደዚህች ዓለም መጣሁ? የእኔ ተልዕኮ ምንድን ነው? ያ ተልዕኮስ የሰው ልጅን ሕይወት ወደ በጎ ምእራፍ የሚለውጥ ነው ወይ? ያንን ተልዕኮስ እያሳካሁት ነው ወይ? የሚለውን ካሰብን፣ ሀገር ብዙ ታላላቅ ሰዎችን ታተርፋለች። የሰው ልጅ ጉዞም መልካምን ጎዳና በሚሠሩ ሰዎች የተነካ የተቃና ይሆናል።

በዚህ የመውሊድ በዓል የሕይወት ተልዕኳችንንና የተልዕኳችንን ስኬት እያስተዋልን በዓሉን እንደምናከብር ተሥፋ አደርጋለሁ። የዘንድሮው በዓል ድርብ በዓል ነው። የዛሬ ሃምሳ ዓመት መጅሊስ የተቋቋመው በመውሊድ በዓል ቀን(ረቢ አል አወል 12ኛ ቀን) ነውና።

በድጋሚ እንኳን ለነቢዩ መሐመድ (ሰዐወ) የልደት በዓል(መውሊድ) እና ለመጅሊስ ሃምሳኛ ዓመት በሰላም አደረሳችሁ።

**ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር!!**

**ፈጣሪ ኢትዮጵያና ሕዝቦቿን ይባርክ!**

**መስከረም 4፣ 2017 ዓ.ም**